**የክርስቶስ ኢየሱስ ማንነት መገንዘብ** (Christ consciousness)

እግዚአብሔር በሶስት ሰብዕና ማለትም በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ለዘላለም እንደሚኖር ከዚህ ቀደም ድረ-ገጽ ላይ በተለቀቀ ትምህርት ተገልጾዋል፡፡ ስለ እግዚአብሔር አብ በብሉይ ኪዳንም ብዙ ስለተነገረ ብዙዎች ማንነቱን ያውቃሉ፡፡ ስለ እግዚአብሔር ወልድና መንፈስ ቅዱስ ማንነት ግን በብሉይ ኪዳን በበቂ ሁኔታ የተብራራ አልነበረም፡፡ ስለዚህ ነው የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና የጌታ መንፈስ ቅዱስ ማንነት መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው የተወሰነ ያህል ማብራራት አስፈላጊ የሆነው፡፡

## 1. ጌታ ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ በሥጋ ከመገለጡ/ከመወለዱ በፊት የነበረው ማንነት (before His incarnation፡)

ጌታ ኢየሱስ ስጋ ለብሶ ወደዚህ ምድር ከመምጣቱና ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የነበረ መሆኑን ራሱ በሚከተሉት የቃሉ ክፍሎች በግልጽ አስተምሯል፡ ዮሐ 3:13; 6:33, 38, 62; 8:23; 58፣ 16:28፣ ዮሐ 17፡5፣ 24

ስለ መሲሁ መምጣት የተነገሩ የትንቢት/የተስፋ ቃሎች የሚመጣው አዳኝ ፍጥረት ሳይሆን አምላክ መሆኑን የሚገልጹ አሉ፡፡ ኢሳ 7፡14፤ 9፡6፣ ማቴ 1፡23፤ (አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከኛ ጋር ነው ማለት ነው)

በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ጌታ ኢየሱስ ከፍጥረታት በፊት የነበረና የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ፣ የመለኮት ፍጹም ሙላት ያለው መሆኑን ይናገራሉ፡፡ {በዚያን ወቅት መጠሪያ ስሙ "ቃል" (ሎጎስ) የሚል ነበር፡፡ በራዕይ መጽሐፍም በተመሳሳይ ስም ተጠርቷል፡፡ ራእይ 19፥13፣ "እርሱ በደም የተነከረ ልብስ ለብሶአል፤ ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ነው።"} ይላል፤

ዮሐ 1፡1-3፣ "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። 2
እርሱም በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ። 3 ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሮአል፤ ከተፈጠረው ሁሉ
ያለ እርሱ የተፈጠረ ምንም የለም።" (1ቆሮ 8፡6፣ ፊሊጵ 2፡5-6፣ ቆላስ 1:15-17; ዕብ 1:1-2፣ ዮሐ 10፡ 17-18፡፡)

የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጌታ ኢየሱስ ከአብ ጋር ከመጀመሪያ ጀምሮ እንደነበር ያሳያሉ፣ 1 ዮሐ 1:2; ገላ 4:4፣ 1ጴጥ 120-21፣ ራዕ 1፡8፤ 2፡8፣

**መጥምቁ ዮሐንስ ከጌታ ኢየሱስ በፊት የተወለደ ሆኖ ሳለ ጌታ ኢየሱስ ከመጥምቁ ዮሐንስ በፊት እንደነበር ተናግሯል፡- ዮሐ 1፥15** "ዮሐንስም፣ "ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ በፊት ስለ ነበረ ከእኔ ይልቃል' ብዬ የመሰከርሁለት እርሱ ነው" በማለት ጮኾ ስለ እርሱ መሰከረ።"

**ጌታ ኢየሱስ ራሱ አብርሃም ከመወለዱ በፊት እንደነበር ተናግሯል፡-**

**ዮሐንስ 8:57-58፤** አይሁድም፣ "ገና አምሳ ዓመት ያልሞላህ፣ አንተ አብርሃምን አይተሃል!" አሉት።

58 ኢየሱስም፣ "እውነት እላችኋለሁ፤ አብርሃም ከመወለዱ በፊት እኔ፣ እኔ ነኝ" አላቸው።

**ጌታ ኢየሱስ ራሱ ሲሰግዱለት ሳይከለክል አምልኮ በመቀበሉ አምላክነቱን የሚያሳዩ ክፍሎች አሉ፤**

ማቴ 28:9, 17; ሉቃ 24:52; ዮሐ 9:38; 20:28፡፡

ከዚህ በላይ የሰፈሩት የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር በመምጣት ሰው ከመሆኑ በፊት ምንም ዓይነት ፍጥረት ሳይፈጠር አስቀድሞ የነበረና ከእግዚአብሔር አብ ጋር ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረ አምላክ መሆኑን የሚያሳዩ ማስረጃዎች ናቸው፡፡

**2. ጌታ ኢየሱስ ሰው ሆኖ ወደ ምድር ከመጣ በኋላ ማንነቱ፡-**

የተጠራባቸው ስሞች፡- መሲሁ(ክርስቶስ)፣ (ዮሐ 12፡27)፣ ጌታ (ማቴ 7፡21)፣ መምህር (ማስተር ሉቃ 5፡ 5)፣ የእግዚአብሔር ልጅ (ማቴ 14፡33)፣ የሰው ልጅ (ማቴ 9፡6)፣ የዳዊት ልጅ፣ የአብርሐም ልጅ፣ (ማቴ 1፡1)፣ የዮሴፍ ልጅ (ዮሐ 1፡45)፣ የእግዚአብሔር በግ (ዮሐ 1፡29)፣ የዓለም ብርሃን (ዮሐ 8፡12)፣ የእስራኤል ንጉስ (ማቴ 27፡42)፣ ረቡኒ (ዮሐ 20፡16)፣ የሕይወት እንጀራ (ዮሐ 6፡35)፣ የበጎች በር (ዮሐ 10፡10፡7፣ 9)፣ መልካም እረኛ (ዮሐ 10፡11)፣ ትንሰኤና ሕይወት (ዮሐ 11፡25)፣ መንገድ፣ እውነትና ሕይወት፤ (ዮሐ 14፡6)፣ ዕውነተኛው የወይን ተክል (ዮሐ 15፡1)፣ መድህን/አዳኝ (ሉቃ 2፡11) …."

**ሰው ሆነ፡-** ከመወለዱ በፊት (ዮሐ 8፡58፣ ዮሐ 1-10፣) ጌታ ኢየሱስ ከእግዚብሔር አብ ጋር በእኩል መለኮታዊ ባህርዩ፣ ዘመን መቆጠር ከመጀመሩ በፊት በቅዱሳን መላእክቱ ሲከበርና ሲመለክ የነበረ አምላክ ነበረ፡፡ በሰማይና በምድር የሚታየውና የማይታየው የፈጠረ ነው፡፡ ወደ ምድር ሲመለከት በኃጢአት ምክንያት ወድቆ በጨለማው ኃይል ክፉ አገዛዝ እየተጨቆነ ያለ፤ ከእርግማን በታች ሆኖ ልዩ ልዩ በሽታና፤ የጦርነት የጉስቁልና ኑሮ ቀንበር ተሸክሞ የዘላለም ሞት ፍርድ ከመጠባበቅ በስተቀር ሌላ አማራጭ ያልነበረው የሰው ዘር ሰቆቃ አየ፡፡

ፍቅሩና ርህራሄው ይህን አይቶ ዝም ማለት ስላላስቻለው መለኮታዊ ከፍታውና ክብሩን ትቶ እጅግ በሚጠላውና በሚጠየፈው ኃጢአት ማጥ የሚዳክር የሰው ዘር ወደ ሞላበት ምድር ከድንግል ማርያም ተጸነሶ ደካማና በስፍራ የሚወሰን የሆነውን ስጋ ለብሶ በግርግም ለመወለድና ሰው ሆኖ ለመምጣት ፈቅዶ እንደ እኛው ስጋ የለበሰ ሰው ሆነ፡፡

ድንግል ማርያም በልዑል እግዚአብሔር ኃይል/በመንፈስ ቅዱስ ስለጸነሰች ምንም የወንዴና ሴቴ ዘር ሳይኖር የእግዚአብሔር ቃል (ዮሐ 1፡1፣ ራዕ 19፡11-13) ይባል የነበረው አምላክ በመለኮታዊ ችሎታው (ከማርያም ስጋ ሳይወስድ) ራሱ ስጋ ሆኖ በማህጸና አደረ፣ ስለዚህ ስጋውም ደሙም ከራሱ ነው፡፡ ኢየሱስ ራሱ ከዚህ ዓለም አይደለሁም ያለው ለዚህ ጭምር ነው፡፡ ዮሐ 1፡14፡፡ ሉቃ 1፡32፣ 35፡፡ በእግዚአብሔር ኃይል/ክንድ አማካይነት በባዶ ማህጸን እንደሚጸነስ አስቀድሞ ትንቢት ተነግሮ ነበር፡፡ ኢሳ 7፡14

ኢሳ 53፡1-2፣ "የሰማነውን ነገር ማን አመነ? የእግዚአብሔርስ ክንድ (ኃይል) ለማን ተገለጠ? ² በፊቱ እንደ ቡቃያ፣ ከደረቅም መሬት እንደ ወጣ ሥር በቀለ፤ የሚስብ ውበት ወይም ግርማ የለውም፤ እንድንወደውም የሚያደርግ መልክ አልነበረውም።"

ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር መጥቶ ከድንግል ማርያም ከመወለዱ በፊት እግዚአብሔር አብ ሙሉ መለኮታዊ ማንነት እንደ ነበረው ሁሉ ጌታ ኢየሱስም ሙሉ መለኮታዊ ማንነት የነበረው መሆኑን ከዚህ ቀደም ብሎ ተገልጾዋል። ወደ ምድር በመጣ ጊዜ ግን በመለኮታዊ ማንነቱ ላይ የሰውን ማንነት ወሰዶ በአንድ ጊዜ ሁለት ማንነት ያሉት አምላክም ሰውም ሆነ (አምላክ-ሰው/God-Man/Theanthropic Man)። እንደዚህ ሙሉ መለኮታዊና ሙሉ የሰው ባህርያት በአንድነት ያለው መሆን በእንግሊዝኛ ሃይፖስታቲክ ዩኒየን (Hypostatic Union) ይሉታል። ጌታ ኢያሱስ እነዚህ ሁለት ዓይነት ባህርያት በአንድነት ያለው ሆኖ ለዘላለም ይቀጥላል። ኢሳ 7:14፣ ዮሐ 1:14፣ ዕብ 1:3፣ 1ዮሐ 4:2፤

ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ በአንዱ አካሉ ውስጥ መለኮታዊና ሰዋዊ ባሕርያቱ ተጣምረዋል። ጌታ ኢየሱስ ሁለት ባህርያት ቢኖረውም ከአንድ ጊዜ በስተቀር ራሱን በብዙ ቁጥር አልተናገረም። ዮሐ 3:11
ይመጣል ተብሎ የተነገረለት መሲህ የመለኮትና የሰው ባህርያት እንደሚኖሩት በትንቢት ተነግሮ ነበር። ኢሳ 9:6፤

***ጌታ ኢየሱስ ሁለት ባህሕርያት ያሉት መሆኑ የሰውን ዘር ለማዳን ያለው ጠቀሜታ***

*ሀ.* ሰው በመሆኑ በሰው ዘር ፈንታ እኛን ወክሎ በአሰቃቂ ቁስል ቆስሎ በመሞት የሞት ፍርዳችንን ቅጣት እርሱ ተቀብሏል። እግዚአብሔር ፍትሃዊ ስለሆነ በደለኛን ሳይቀጣ ስለማይተው ስለ ሰው ዘር ኃጢአት ራሱ ሰው ቅጣት መቀበል ስላለበት ጌታ ኢየሱስ ሰው በመሆን ለኃጢአታችን የተገባ የሞት ፍርድ ቅጣት እርሱ ተቀጣ። (ዘኁ 14:18)

*ለ.* በመለኮታዊነቱ የእርሱ ሞት ብዙዎችን ለማዳን መለኮታዊ የሆነ ወሰን የሌለው ታላቅ ዋጋ ያለው ሆኗል።

1ኛ ጴጥሮስ 1:18፣ ከቀድሞ አባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከንቱ ከሆነ ሕይወት የተዋጃችሁት በሚጠፋ ነገር፣ በብር ወይም በወርቅ እንዳልሆነ ታውቃላችሁ፤ (ያለው ለዚህ ነው)፤

*ሐ.* ሁለት ባሕርያት ያለው በመሆኑ ጌታ ኢሱስ በአምላክነቱ ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይሞት ሊቀ-ካህናታችን እንዲሆነን አስችሏል።

*ዕብ* 7:23-25፣ በአገልግሎታቸው እንዳይቀጥሉ ሞት ስለ ከለከላቸው፣ የቀድሞዎቹ ካህናት ቊጥራቸው ብዙ ነበር፤ [24] ኢየሱስ ግን ለዘላለም የሚኖር በመሆኑ፣ ክህነቱ የማይሻር ነው። “ስለዚህ ስለ እነርሱ እየማለደ ሁል ጊዜ በሕይወት ስለሚኖር፣ በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።”

*መ.* ጌታ ኢየሱስ በተቃዋሚዎችና በዲያብሎስ እስከ መስቀል ሞት ድረስ ብዙ ውጊያና ፈተና ደርሶበታል። እንደ እኛው ስጋ የለበሰ በመሆኑ ተርቧል፣ ተጠምቷል፣ በብርድ በረጅም የእግር ጉዞ ደክሟል። ስለዚህ የኛ የሰዎች ድካም ምን ያህል እንደሆነ ራሱ በተለያየ ፈተና በማለፉ ሙሉ በሙሉ ስለሚረዳው ይራራልናል ያግዘንማል። ዕብ 4:15፤

***ታላቅ መምህርና የእግዚአብሔር መንግስት ወንጌል ሰባኪነቱ፡*** - ጌታ ኢየሱስ 30 ዓመት እስከሚሞላው ድረስ እንደ እግዚአብሔር ታላቅ አገልጋይነት ማንም አላወቀውም ነበር፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የጀመረው አገልግሎት በብዛት በጥራት በክብርና በኃይል እየጨመረ ሄደ፡፡ የእግዚአብሔርን መንግስት ወንጌል በእስራኤል ምድር በተለያዩ ቦታዎች በመዘዋወር ሰበከ፡፡ እርሱ ይመጣል ተብሎ ይጠበቅ የነበረው መሲሁ መሆኑን ገልጦ እየተናገረ በእርሱ አምነው እንዲድኑ ጥሪ አደረገ፡፡

*ዮሐንስ 8፡23-24፣ እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፤ “እናንተ ከታች ናችሁ፤ እኔ ከላይ ነኝ፤ እናንተ ከዚህ ዓለም ናችሁ፤ እኔ ከዚህ ዓለም አይደለሁም። [24] በኀጢአታችሁ እንደምትሞቱ ነግሬአችኋለሁ፤ እኔ እርሱ ነኝ ስላችሁ እኔ እርሱ እንደሆንሁ ካላመናችሁ፣ በኀጢአታችሁ ትሞታላችሁና።”*

ለሶስት ዓመታት ያህል ከደቀ መዛሙርቱ መካከል አስራ ሁለቱን መርጦ በየቀኑ ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ በማድረግ የእርሱ መሲህነት/አዳኝነት ምስክሮች እንዲሆኑና እንዴት መኖር እንዳለባቸው ያዘዛቸውን ለሌሎች እንዲያስተምሩ አሰለጠናቸው፡፡

***የዓለም ብርሃን ሆነ፡*** -

*ጌታ ኢየሱስ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ያለው ሰው ሆኖ ሳለ ምንም ኃጢአት የሌለበት መሆኑ፣ መልካም ተግባራትን በማከናውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሁሉ በማድረግ ሙሉ በሙሉ የታዘዘና እጅግ ከባድ የሆነ መከራና ስቃይ ቢደርስበትም በመታገስ የጸናና በክፉ ፈንታ መልካም በመመለስ ለሰው ዘር ሁሉ መልካም ምሰሌነቱን የተወልን ስለሆነ እርሱን በመመሰል እንድንኖር ለማስቻል ነው፡፡*

*ዮሐ 8÷12 “ኢየሱስ እንደ ገና ለሰዎቹ፣ “እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝም የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ ከቶ በጨለማ አይመላለስም” አላቸው።”*

*ዮሐንስ 6÷38 “ከሰማይ የወረድሁት የራሴን ፈቃድ ለማድረግ ሳይሆን፣ የላከኝን የእርሱን ፈቃድ ለመፈጸም ነውና፤”*

*ዮሐ 13፡4-5፣ ከእራት ተነሣ፤ መጐናጸፊያውን አስቀመጠ፤ ወገቡንም በፎጣ ታጠቀ። [5] ከዚያም በመታጠቢያው ውሃ ጨምሮ የደቀ መዛሙርቱን እግር እያጠበ በታጠቀው ፎጣ ያብስ ጀመር።*

ፊልጵስዩስ 2፡6-8፣ እርሱ በባሕርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን ሊለቀው እንደማይገባ አድርጎ አልቈጠረውም፤ [7] ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ፣ በሰውም አምሳል ተገኝቶ፣ ራሱን ባዶ አደረገ፤ [8] ሰው ሆኖ ተገልጦም፣ ራሱን ዝቅ አደረገ፤ እስከ ሞት፣ ያውም በመስቀል ላይ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ።

በምድር የአገልግሎቱ ዘመን ከጥቂት ነገሮች በስተቀር መንፈስ ቅዱስ እንደ ተሞላና በመንፈስ እንደሚመራ፣ ሆነ ብሎ ራሱን ለእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳስገዛ ሰው፣ እንደ ሰው ዘር፣ እንደ አብርሐም ልጅ፣ እንደ ዳዊት ዘር ኖረ እንጂ መለኮታዊ ኃይሉን ባለመጠቀም ራሱን ባዶ አደረገ፡፡ ፊሊጵ 2፡6-8

በሕጻንነት ዕድሜው ሄሮድስ ሊያስገድለው ስለ ፈለገ ከሰሜናዊው እስራኤል በገሊላ ከምትገኘው ናዝሬት በመነሳት ወደ ግብጽ ተሰደደ፡፡ በዚህ ጊዜ የተጓዘው መንገድ ርዝመት ቢያንስ 800 ኪሎ ሜትር ስለሚሆን ያን ያህል ርቀት ለመጓዝ ሳምንታት እንደ ፈጀበት ይገመታል፡፡ ለ3 ዓመት ተኩል በስደት ከቆየ በኋላ ከግብጽ ሲመለስም ያንኑ ርቀት ምድረ-በዳ ባለው መንገድ ተጓጉዟል፡፡

ተራ ሰው ከሚኖረው አይነት ኑሮ በታች ኖረ፡፡ ከኃጢአት በስተቀር በሁሉም ነገር እንደኛው ተፈተነ፡፡ ተራበ ተጠማ፣ በቀትር ሙቀት በሌሊት ቅዝቃዜ ተጎዳ፡፡ አርባ ቀንና ሌሊት በምድረ-በዳ በጾምና በጸሎት ቆይቶ እንደ ተራበ አዳምና ሄዋንን በማሳት የጣለው ዲያብሎስ ሊፈትነው ቀርቦ ብዙ የተፈታተነው በመጎዳቱ ላይ የባሰ ጉዳት በመጨመር ለማሳት ቢሆንም ድል ነስቶ ለጊዜው አራቀው፡፡ ብዙ ጊዜ ቀኑን ሙሉ ብዙ ሕዝብ እያገለገለ ውሎ ሌሊቱንም መሉ ሲጸልይ ያድር ነበር፡፡

> ከሰው ዘር ሁሉ የእግዚአብሔርን ሕግና ፈቃድ ሙሉ በሙሉ ምንም ሳያዛባ መፈጸም የቻለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፡፡ በብዙ ዓይነት ፈተና ቢፈተንም አንዳች ኃጢአት አላደረገም፡፡ ይሄ ብቻ ሳይሆን በብሉይ ኪዳን ያልተጻፈ ሕይወቱን ስለብዙዎች ኃጢአት ስርየት መስዋዕት አድርጎ እስከ መስጠት ድረስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያደረገና አብ የሰጠውን ሥራ ሁሉ የፈጸመ ነው፡፡ ዮሐንስ 17፡4-5፣ "የሰጠኸኝን ሥራ በመፈጸም በምድር አከበርሁህ። [5] እንግዲህ አባት ሆይ፤ ዓለም ሳይፈጠር ከአንተ ጋር በነበረኝ ክብር በአንተ ዘንድ አክብረኝ።"
> ሁሉም ያለው ሆኖ ሳለ አንዳች የሌለው ድሃ ሆነ፡፡ ሉቃ 9፡58፣ 8፡20፣ 2ቆሮ 6፡9
> የመለኮት ሙላትና ክብር ያለው ሆኖ ሳለ የፈጠረው ሰው አገልጋይ ሆኖ የደቀ-መዛሙርቱን እግር አጠበ፡፡ ማር 10፡45፣ ዮሐ 13፡4-7፡፡

በዚህ ሁሉ መልካም በማድረግ በቅድስና ተመላለሰ እንጂ ኃጢአት አልተገኘበትም፡፡ የተከሰሰው የኃጢአተኞች ወዳጅ ሆነ፤ በሰንበት ፈወሰ (መልካም አደረገ)፤ የእግዘዚአብሔር ልጅ ነኝ በማለት ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካከለ … ወዘተ በሚል ነበር፡፡

እርሱ ግን ሁሌ ትክክለኛ አሳብ አሰበ፡ ሁሌ ትክክለኛ ቃል/ንግግር ተናገረ፣ ሁሌ መልካም ስራ አከናወነ፤ ሁሌ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አደረገ፤ ሁሌ በተገቢ ስፍራ ተገኘ፡፡

ጌታ ኢየሱስ አምላክ ሆኖ ሳለ ሆነ ብሎ ራሱን ዝቅ አድርጎ በሰው አምሳል ተገኝቶ ከላይ የተዘረዘረው ሁሉ ውርደት፣ መከራና ሥቃይ የተቀበለውና የጽድቅ ሥራ ያከናወነው በእርሱ የሚያምን የሰው ዘር ሁሉ የእርሱ ጽደቅ ሆኖ እንዲቆጠርለት ለማስቻል ነው፡፡ 1ቆሮ 1፡29-31፣

**አዳኝ ሆነ፡- በእርሱ የሚያምኑትን የዓለም ሕዝብ ሁሉ ጠላቶቻቸው ከሆኑት ከሥራ ሕግና ከኃጢአት፣ ከበሽታና ከእርግማን ሁሉ፣ ከዲያብሎስና አጋንንቱ እንዲሁም ከዘላለም ሞት የሚያድን አዳኝና ነጻ አውጪ ነው፡፡**

ማቴ 1፥21 "ወንድ ልጅ ትወልዳለች፤ ስሙንም ኢየሱስ ብለህ ትጠራዋለህ፤ ሕዝቡን ከኀጢአታቸው ያድናቸዋልና።"

ሉቃ 2፡8-11፣ በዚያው አገር በሌሊት መንጋቸውን ሲጠብቁ በሜዳ የሚያድሩ እረኞች ነበሩ። [9] የጌታም መልአክ ድንገት መጥቶ በአጠገባቸው ቆመ፤ የጌታም ክብር በዙሪያቸው አበራ፤ ታላቅም ፍርሀት ያዛቸው። [10] መልአኩ ግን እንዲህ አላቸው፤ "አትፍሩ፤ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች አምጥቼላችኋለሁና። [11] ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኅን ተወልዶላችኋልና፤ እርሱም ጌታ ክርስቶስ ነው።

ሉቃስ 4፡18-21፣ "የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለድኾች ወንጌልን እንድሰብክ፣ እርሱ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩት መፈታትን፣ ለታወሩትም ማየትን እንዳውጅ፣ የተጨቈኑትን ነጻ እንዳወጣ፣ [19] የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እንዳውጅ ልኮኛል።" [20] ከዚያም መጽሐፉን ጠቅልሎ ለአገልጋዩ መልሶ ሰጠውና ተቀመጠ፤ በምኵራብ የነበሩትም ሁሉ ትኵር ብለው ይመለከቱት ነበር። [21] እርሱም፣ "ይህ በጆሮአችሁ የሰማችሁት የመጽሐፍ ቃል ዛሬ ተፈጸመ" ይላቸው ጀመር።

ዮሐ 8፥36፣ "እንግዲህ ወልድ ነጻ ካወጣችሁ፣ በእውነት ነጻ ትሆናላችሁ።"

ጌታ ኢየሱስ የሰው ዘርን ለማዳን ስለመጣ በአጋንንት የታሰሩትን ነጻ አወጣ፣ በልዩ ልዩ በሽታዎች የተጠቁትን ፈወሰ፣ ዲዳዎች ተናገሩ፣ ደንቆሮዎችና ሽባዎች ፈወሳቸው፣ አንካሳዎች ዘለሉ፣ የታወሩ ዓይኖችን አበራ፣ ለምጻሞችን አነጻ፣ የሞተን አሰነሳ፣ ሞቶ የተቀበረን ከቀናት በኋላ አስነስቶ በህይወት አኖረ፡፡ ሰው ከእነዚህ ዓይነት ችግሮችና ጠላቶች ስለ ተገላገለ ብቻ ነጻነቱ ተቀዳጀ አያሰኝም፡፡ ምክንየቱም የሰው ዘር ጠላቶች እነዚህ ብቻ አይደሉምና፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሙሉ ነጻነት ያገናጸፈን እንደ መስዋዕት በግ ተሰውቶ በቀራንዮ መስቀል ላይ በከፈለልን ታላቅ ዋጋ ነው፡፡

ጌታ ኢየሱስ እስከ መስቀል ሞት ድረስ የከፈለው ዋጋ የዓለምን ሕዝብ ሁሉ ኃጢአት ማስተሰረይና የዘላለም ሕይወት ማግኘት የሚያስችል ስለ ሆነ ይህንን ዓይነት ታላቅ የማዳን ስራ ከእርሱ በስተቀር የትኛውም ፍጥረት ሊያከናውን ስለ ማይችል መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ገልጾታል፤

ሐሥ 4፥12፣ "ድነት በሌላ በማንም አይገኝም፤ እንድንበት ዘንድ ለሰዎች የተሰጠ ከዚህ ስም በስተቀር ሌላ ስም ከሰማይ በታች የለምና።"

**የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ሆነ፡ -** ጌታ ኢየሱስ ከላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣ፣ በገዛ ፈቃዱ ስለ እኛ ሕይወቱን አሳልፎ እንደሚሰጥና እንደሚሞት ደግሞም በራሱ ኃይል ከሞት እንደሚነሳ አስቀድሞ መናገሩን የሚያሳዩ ጥቅሶች ጥቂቶቹ እነሆ፡፡ (ራዕ 5፡9-10፣13፡8፣ )

*ዮሐ 10፡17-18፣ መልሼ ለማንሣት ሕይወቴን አሳልፌ ስለምሰጥ አባቴ ይወደኛል።[18] ሕይወቴን በራሴ ፈቃድ አሳልፌ እሰጣለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም፤ አሳልፌ ለመስጠትም ሆነ ለማንሣት ሥልጣን አለኝ፤ ይህን ትእዛዝ የተቀበልሁትም ከአባቴ ነው።" (ሉቃ 9፡22)*

*ዮሐ 3፡[14] ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ፣ የሰው ልጅም እንዲሁ ሊሰቀል ይገባዋል፤*

*ዮሐ 1፥29 "ዮሐንስ በማግሥቱ፣ ኢየሱስ ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፤ "እነሆ! የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ፤"*

*1 ቆሮ 5፥7፡፡ "አሁን ያለ እርሾ እንደሆናችሁ ሁሉ አዲስ ሊጥ እንድትሆኑ አሮጌውን እርሾ አስወግዱ፤ የፋሲካ በጋችን የሆነው ክርስቶስ ተሠውቶአልና።"*

በጌተሰማኔ ሊገድሉት በሚፈልጉት ጠላቶቹ ከመያዙ በፊት ከጥቂት ሰዓታት በኋላ የሚደርስበት ታላቅ ስቃይና መከራ አውቆ እጅግ ተጨንቆ ላቡ እንደ ደም ነጠብጣብ ይፈስ ነበር፡፡

እጅግ ብዙ በሆነው መልካም ተግባሩ ፈንታ የአይሁድ ሃይማኖት መሪዎችና ተባባሪዎቻቸው ጋኔን ያደረበት እብድ (ዮሐ 10:20)፣ አሳች (ሉቃ 23:2)፣ ወንጀለኛ (ዮሐ 18:30)፣ አሉት፤ አፌዙበት፣ ተፉበት፣ ደበደቡት፣ በጅራፍ አስገረፉት፡፡ ምንም ኃጢአት ሳይኖርበት እንደ ሚታረድ በግ፣ እንደ አደገኛ አመጸኛ ተይዞ/ታስሮ ምሽት በጭለማ ተነዳ፡፡ ለፍርድ ችሎት ቀረበ፤ እንደ አደገኛ ወንጀለኛ ተገርፎ ተመረመረ፤ ልብሱን ገፈፉት፡፡ ነገር ግን እርሱ ይህን ያህል ላዋረዱትና የከፋ ክፋት ለፈጸሙበት ጠላቶቹ ማለደ፡፡

*ሉቃ 23፥34፣ "ኢየሱስም፣ "አባት ሆይ፤ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" አለ። እነርሱም ልብሱን በዕጣ ተከፋፈሉት።"*

በመጨረሻም በእንጨት መስቀል ላይ ሰቅለው መልካም ያደረገባቸው እጆቹና እግሮቹ መስቀሉ ላይ በምስማር ቸንክረው፣ ለመዘባበቻ ራሱ ላይ የሾህ አክሊል ደፍተውበት፣ ጎኑን በጦር ወግተው ስለ ገደሉት እንደ ሰው በስጋ ሞቶ ተቀበረ፡፡ በዚህ ሁኔታ ኃጢአታችንና እርግማናችንን ከኛ ወስዶ በመሸከሙ ለእኛ የተገባውን እጅግ አሰቃቂ መከራና ሰቆቃ አድርሰውበት የሞት ቅጣት ፍርዳችንን እርሱ ተቀበለ፡፡ ስለ በጎቹ ሕይወቱን አሳልፎ መልካም እረኛነቱን በዚህ ሁኔታ አረጋገጠ፡፡

ተቃዋሚዎቹ ብቻ ሳይሆን ቤተሰቦቹ ከተልዕኮው ወደኋላ እንዲመለስ መሻት ነበራቸው እንጂ እሰይ አበጀህ አላሉትም፤ ብዙዎች እርሱ የሚናገረውን ለመስማት ይፈልጉት እንደ ነበረው ቤተሰቦቹ አላደረጉም፡፡ አብዷል ብለው ይዘውት ወደ ቤታቸው ሊመለሱ የፈለጉበት ጊዜ ነበር (ማር 3፡21-22፣ 31-35)፡፡ ደቀ-መዛሙርቱም የሚደርስበትን መከራ ባጭሩ ሲነግራቸው ይኸማ ባንተ አይድረስ ብለውታል፤ የሚነግራቸውንም በአግባቡ አልተረዱትም፡፡ የመስቀል መከራ ሲቀበል ከደቀመዛሙርቱ ሁሉ ከጎኑ የቆመ የለም፡፡

ለ33 ዓመታት ያህል በዚህ ዓይነት ባልተቋረጠ እጅግ ከባድ ውጊያ ያለፈበት ብቸኛ ምክንያት ለእግዚአብሔር አብ ክብርና ለእኛ ለሰው ዘሮች መዳን ለማስገኘት ነው፡፡ ክብር ለዘላለም ለስሙ ይሁን፡፡

**ትንሳኤና ሕይወት** ነው፡- ሞቶ ከተቀበረ በኋላ ወደ ሲኦል ወረደ፡፡ የሰው ዘር ሁሉ ዋነኛ ጠላት የሆኑት ሞትና ዲያብሎስን ወደ ማጥቃት ተሸጋግሮ በድል አድራጊነት አጠናቀቀ፡፡ ሞቶ በተቀበረ በሶስተኛው ቀን ሌሎች ሙታንን ከሞት ማስነሳት ብቻ ሳይሆን ራሱ ከሙታን መነሳት የሚችል መሆኑን በማሳየት ከሙታን ተነሳ፡፡ በውሀ ላይ መራመድ የቻለ ብቻ ሳይሆን በአየሩ እየተንሳፈፈ ወደ ሰማይ አርጎ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ከመቀመጡ በፊት እርሱ ወዳለበት ሊወስደን ተመልሶ እንደሚመጣ ተናገረ፡፡

*ይሄ ብቻ ሳይሆን ጌታ ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር አብ የሚያደርስ መንገድና ዙፋኑም ወዳለበት ቅድስተ-ቅዱሳን የሚያስገባ በር፣ ዕውነትና ሕይወትም ነው፡፡*

ዮሐ 14፡5-6፣ ቶማስም፣ “ጌታ ሆይ፤ ወዴት እንደምትሄድ አናውቅም፤ ታዲያ፣ መንገዱን እንዴት ማወቅ እንችላለን?” አለው። [6] ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ “መንገዱ እኔ ነኝ፤ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ፤ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።

ዮሐ 10፥9፣ “በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ በኩል የሚገባ ሁሉ ይድናል፤ ይገባል፤ ይወጣልም፤ መሰማሪያም ያገኛል።”

**ጌታ ኢየሱሰ ክርስቶስ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል አስታራቂ /አማላጃችን/ እንደሆነ የሚያሳዩ ጥቅሶች፡-**

ሮሜ 8፡33-34፣ “እግዚአብሔር የመረጣቸውን የሚከስ ማን ነው? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፤ታዲያ የሚኰንን ማን ነው? **የሞተው፣ እንዲሁም ከሞት የተነሣው፣ በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው ክርስቶስ ኢየሱስ፣ ስለ እኛ ይማልዳል።”**

1 ዮሐ 2፥1፣ “ልጆቼ ሆይ፤ ይህን የምጽፍላችሁ ኀጢአት እንዳትሠሩ ነው፤ **ነገር ግን ማንም ኀጢአት ቢሠራ፣ በአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፤ እርሱም ጻድቁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።”**

ሉቃ 22፡31-32፣ ጌታም፦ ስምዖን ስምዖን ሆይ፥ እነሆ፥ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ [32] **እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ (ጸለይሁ)**፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና አለ።

ዕብ 7፡23-25፣ [23] እነርሱም እንዳይኖሩ ሞት ስለ ከለከላቸው ካህናት የሆኑት ብዙ ናቸው፤ [24] እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው፤ [25] ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።

ዕብ 8፡1-2፣ እንግዲህ የምንናገረው ዋናው ነገር ይህ ነው፤ በሰማያት በግርማው ዙፋን ቀኝ የተቀመጠ እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት አለን፤ [2] እርሱም በሰው ሳይሆን በጌታ በተተከለችው፣ እውነተኛ ድንኳን በሆነችው ቤተ መቅደስ አገልጋይ ነው። (ዕብ 7፡26-27፣ ዕብ 10፡10፣ ዕብ 10፡14፣)

ዕብ 9፡12-14፣ “የገባውም የፍየልንና የጥጃዎችን ደም ይዞ አይደለም፤ ነገር ግን የዘላለም ቤዛነት ሊያስገኝ የራሱን ደም ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ገባ።”

ዕብ 9፡22፣ “በርግጥ ከጥቂት ነገሮች በስተቀር ሁሉም ነገር በደም መንጻት እንዳለበት ሕጉ ያዛል፤ **ደም ሳይፈስ ስርየት የለምና።”**

ዕብ 12፥24፣ “የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ወደ ሆነው ወደ ኢየሱስ፣ እንዲሁም ከአቤል ደም የተሻለ ቃል ወደሚናገረው ወደ ተረጨው ደም ደርሳችኋል።”

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ሥጋ ለብሶ በተመላለሰበት ጊዜ በስሙ ለተጠሩት ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ስለ ተቃዋሚዎቹም ይማልድ ነበር። አሁንም በእግዚአብሔር አብ ዙፋን ቀኝ ስለተቀመጠ ስለ ሕዝቡ ኃጠአት ሁሌ ይማልዳል። ሰይጣንም ሕዝቡን በሚከስበት ጊዜ የሕዝቡ ጠበቃ ሆኖ የሚሟገት ነው። ወደ ፊትም የዓለም ፍጻሜ እስከሚሆን ድረስ በእግዚአብሔር ፊት የሕዝቡ አማላጅነት ይቀጥላል። ጌታ ኢየሱሰ ስለ ሕዝቡ ይማልዳል/ይሚገታል ሲባል ግን እያንዳንዱ አማኝ ኃጢአት በሰራ ቁጥር ስለ እያንዳንዱ ሰው በእግዚአብሔር አብ ፊት እያጎነበሰ ተንበርክኮ እያለቀሰ ይቅር በለው እያለ ይለምናል ማለት አይደለም። በጎልጎታ መስቀል ላይ ተሰቅሎ በመሰቃየት ደሙን በማፍሰስ በሞተበት ጊዜ ሁሉን ሥራ ሰርቶ ስለጨረሰ ያ ወደ ሰማያዊቱ የእግዚአብሔር መቅደስ ይዞት የገባው የሚናገረው የራሱ ደም ዛሬና ዘወትር የዓለም ፍጻሜ

እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ ትኩስ ሆኖ የመናገርና የሕዝቡን ኃጢአት የማስተሰረይ ብቃት ስላለውና የማንጻት ተግባር ስለሚያከናውን ነው፡፡

### 3. የጌታ ኢየሱስ ማንነት ከትንሳኤው በኋላ ታላቅ ኃይልና ክብር የተላበሰ መሆኑን የሚያስረዱ የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች፡-

1ኛ ጢሞ 3፥16፣ "የእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ምስጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፤ እርሱ በሥጋ ተገለጠ፤ በመንፈስ ጸደቀ፤ በመላእክት ታየ፤ በአሕዛብ ዘንድ ተሰበከ፤ በዓለም ባሉት ታመነ፤ በክብር ዐረገ።"

ዕብ 1፡1-4 "እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በተለያየ ጊዜና በልዩ ልዩ መንገድ በነቢያት በኩል ለአባቶቻችን ተናግሮ፣ [2] በዚህ መጨረሻ ዘመን ግን ሁሉን ወራሽ ባደረገውና ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ ለእኛ ተናገረን። [3] እርሱ የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅ ቅና የባሕርዩ ትክክለኛ ምሳሌ ሆኖ፣ በኀያል ቃሉ ሁሉን ደግፎ ይዞአል፤ የኀጢአት መንጻት ካስገኘ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ። [4] ስለዚህ የወረሰው ስም ከመላእክት ስም እንደሚበልጥ ሁሉ፣ እርሱም ከመላእክት እጅግ የላቀ ሆኖአል።"

ራዕ 1፡12-18፣ "እኔም የሚናገረኝን ድምፅ ለማየት ዞር አልሁ፤ ዞር ባልሁም ጊዜ ሰባት የወርቅ መቅረዞችን አየሁ፤ [13] በመቅረዞቹም መካከል "የሰው ልጅ የሚመስል" አየሁ፤ እርሱም እስከ እግሩ የሚደርስ መጐናጸፊያ የለበሰ፣ ደረቱንም በወርቅ መታጠቂያ የታጠቀ ነበር። [14] ራሱና ጠጕሩም እንደ ነጭ የበግ ጠጕር፣ እንደ በረዶም ነጭ ነበሩ፤ ዐይኖቹም የእሳት ነበልባል ይመስሉ ነበር። [15] እግሮቹ በእቶን እሳት የጋለ ናስ ይመስሉ ነበር፤ ድምፁም እንደ ብዙ ወራጅ ውሃ ድምፅ ነበረ። [16] በቀኝ እጁ ሰባት ከዋክብት ይዞ ነበር፤ ከአፉም በሁለት በኩል የተሳለ ሰይፍ ይወጣ ነበር፤ ፊቱም በሙሉ ድምቀቱ እንደሚያበራ ፀሓይ ነበረ።[17] ባየሁት ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ በእግሩ ሥር ወደቅሁ። እርሱም ቀኝ እጁን በላዬ ጭኖ እንዲህ አለኝ፤ "አትፍራ፤ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም እኔ ነኝ፤ [18] እኔ ሕያው ነኝ፤ ሞቼ ነበር፤ እነሆ አሁን ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፤ የሞትና የሲኦል መክፈቻም በእጄ ነው።"

ራእይ 1፥8፣ "ያለውና የነበረው፣ የሚመጣውም፣ ሁሉን ቻይ ጌታ አምላክ፣ አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ" ይላል።"

ራእይ 19፥16፣ "በልብሱና በጭኑ ላይ እንዲህ የሚል ስም ተጽፎአል፤ "የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ።"

ራዕ 3፡7፣ እውነት የሆነ የዳዊት መክፈቻ ያለው እርሱ የዘጋውን ማንም የማይከፍት፤ እርሱ የከፈተውን ማንም ሊዘጋ የማይችል፡፡

ራዕ 5፡1-10፣ በሰባት ማህተም የተዘጋውን መጽሐፍ ሊከፍት የሚችል ከይሁዳ ነገድ የሆነ አንበሳ ጌታ ኢየሱስ ብቻ ተገኘ፡፡

ራዕ 22፡12-13፣ "እነሆ፤ ቶሎ እመጣለሁ፤ ዋጋዬ በእኔ ዘንድ አለ፤ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍለዋለሁ። [13] አልፋና ዖሜጋ፣ ፊተኛውና ኋለኛው፣ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ።

ማቴ 28፥18 "ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱ ወዳሉበት ቀርቦ እንዲህ አላቸው፤ "ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል፤" (ኤፌ 1፡20-22፣ ፊሊጵ 2፡9-1፣ ቆላ 2፡9-10፣ ቆላ 2፡14-15፣ ዕብ 2፡14-15፣)